# የግብርና ምኒስተሩ ተግባር መሬት መሸጥ ሳይሆን ህዝቡ በምግብ ዋስትና እንዲኖረው ያልተቆጠበ ጥረት ማድረግ ነው !

ካለፉት ስድስት ዐመታት ጀምሮ የኢህአዴግ አገዛዝ የውጭ „ኢንቬስተሮችን“ ለመሳብና የእርሻውን መስክ „ዘመናዊ“ ለማድረግ በሚል በብዙ ሚሊዮን ጋሻ የሚቆጠር -ሶስት ሚሊዮንን ሄክታር- መሬት ለቻይና ፣ ለህንድ ፣ ለሳውዲ አረብያ ፣ ለጂቡቲ... ወዘተ. „እንዳከራየ“(እንድሸጠ) እንዲሁም ለመሸጥ እንደተዘጋጀ ይታወቃል። በዚህ አንዳንዱ ቤልጅግን የሚያክል መሬት ፣ ስንዴ ፣ በቆሎ ፣ ሩዝ ፣ ሰሊጥ ፣ ሽንኮራገዳ ፣ ለነዳጅ የሚሆን ዘርና አበባ ፣ እንዲሁም ልዩ ልዩ አትክልቶች እየበቀሉ የወጭ ምንዛሪ ለማግኘት በሚል ሳቢያ በቀጥታ ወደነዚህ አገሮች ይጫናሉ። የኢህአዴግ አገዛዝ ይህንን አገርን የመቸብቸብ እርመጃ ሲወስድ የውስጥ ለውስጥ በራሱ ተነሳሽነት የሚፍጽመው ድርጊት እንጂ ህገ-መንግስቱ ስለሚፈቅድ ወይም ፓርሊያሜንት ውስጥ ውይይት ተደርጎበትና ተመክሮበትና እንዲሁም በደንብ ተጠንቶ አይደለም። ይህ በኢህኢዴግ አገዛዝና ለጊዜውም ቢሆን አልፎልናል ብለው በሚንደላቀቁ ጊዜ አመጣሽ ግለሰቦችም ሆኑ ቡድኖች የሚካሄደው አገርን የመቸብቸብ ድርጊት በቀላሉ ሊወገድ የማይችል የፖለቲካ ፣ የማህበራዊ ፣ የኢኮኖሚ ፣ የባህልና የአካባቢ ቀውስ ጥሎ እንደሚያልፍ መታውቅ አለብት።

እንደሚታወቀው አንድ አገር የረዥም ጊዜ ሂደት ውጤት ነው። የዛሬይቱን ኢትዮጵያ በአንድ ሰንድቅ ዓላማ ስር ለማደራጀትና እንደ ህብረተሰብ ለመመስረት እናቶቻችንና አባቶቻችን በተለያዩ ጊዜያት አገራችንን ለመወረርና ቅኝ ግዛት ለማድረግ የመጡትን ኃይሎች እየመከቱ መልሰዋል። የተከታታዩ ትውልድ ተግባርና ኃላፊነት የጎደለውን እያስተካከለ ለመጪው ትውልድ የበለጠ ጠንካራ አገር ማስተላለፍ ሲገባው በዚህም በዚያም ብሎ አገርን ማዳከምና ለውጭ ኃይሎች መንብርከክ እንደ ትልቅ ሙያ ተወስዷል። ካለፉት ሃያ ዐመታት ዠምሮ በተለያዩ አቅጣጫዎች አገርን የማዳከሙ ተግባር ከየት እንደመጣና ለጊዜያዊ ጥቅም ተብሎ አገርን መቸብቸብ እንደቁም ነገር መወሰዱ በቀላል ቋንቋ ሊገለጽ የሚችል አይደለም። ከኢኮኖሚ አንፃር ታስቦ ነው ከተባለ ገንዘብ ውስጣዊ ይዘት(Intrinsic Value) የሌለው እንደ ቅጠል መታየት ያለብትና ዋጋ ሊኖረው የሚቸለው በቀጥታ ከቴክኖሎጂና ከተከታታይ የምርት ክንውን ጋር የተያያዘ እንደሆን ብቻ ነው። ተጨባጩ የአገራችን ሁኔታ የሚያሳየው ግን መሬት የሚቸበቸበው ገንዘብ ለማግኘት ተብሎ ብቻ ነው። ገንዘብ ለማግኘት ከተፈለገ ደግሞ ራሱ መንግስትና ህዝብ ቢሰሩበትና ቢታወቀብት ለጠቅላላው ህዝብ የሚጠቅም ከወጭ ከሚገኘው ገንዘብ የበለጠ ሀብት ማፍራት ይቻላል።

ተቀማጭነቱ ሰሜን አሜሪካ በሆነው በኢትዮጵያን ሪቪው ድህረ-ገጽ ላይ ሰሞኑን ለንባብ በቀረበው አጠር መጠን ያለ ገለጻ የኢህአዴግ አገዛዝና ተወካዩ የእርሻ ምኒስተር ባለስልጣን የሆነው አቶ ተፈራ ደርበው ቬርዳንታ ሃርበስተስ ለተባለ አንድ የህንድ ኩባንያ አንድ ሚሊዮን ስምንት መቶ ሺህ ሄክታር መሬት እንደሸጠ ይታወቃል። መሬትን የየአካባቢው ህዝብ ሳይመክርበትና ሳይስማማበት መሸጡ ህዝቡን አስቆጥቶታል። ከልባቸው ይሁን ከአንገት በላይ የህዝቡ ብሶት ተደማጭነት አለው ለማለት ያህል የአገሪቱ ፕሬዚደንት የሆኑት መቶ አለቃ ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ በጋምቤላ ክልል መሬትን ለመሸጥ እየተካሄደ ያለው ተግባር እንዲቆም ለእርሻ ምኒስተሩ ደብዳቤ ቢጽፉም የተሰጣችው መልስ አሉታዊ ነው። እንደዚህ ዐይነቱን አገርን የመቸብቸቡ ጉዳይ አብዛኛውን ጊዜ የሚነሳውና ለጥያቄ የሚቀርበው ወደ ፊት ከኢህአዴግ ስልጣን ተረክበን አገር እናስትዳድራለን ፣ ዲሞክራሲን እናሰፍናለን በሚሉት ተቃዋሚ ኃይሎችና በፓርላሜንት ውስጥ በተቀመጡትና

የህዝብ ተወካይ ነን በሚሉት ፓርቲዎች ሳይሆን ፣ ነገሩ በሚመለከታቸው የውጭ አገር ድርጅቶች የሚነሳና ሰፊ ሀተታ የሚሰጥበት ነው።

## በግብዣ ቅኝ ግዛት አድርጉኝ ጥሪ !

በውጭ አገር ድርጅቶችና ለአፈሪቃ ተቆርቋሪ በሆኑ ግለሰቦች በየጊዜው የሚነሳው ውይይትና ጥያቄ እንዲሁም የሚያስገርማቸው ይህ ዐይነቱ በአፍሪቃ መሪዎች አህጉሪቱን ለውጭ በዝባዦችና ዘራፊዎች አሳልፎ መሸጥና በምሁሩም ዘንድ ዝም ብሎ መታለፉ ነው። አንዳንዶቹንም የመሪዎችን የማሰብ ኃይል እንዲጠራጠሩና ምናልባትም ይሚጎላቸው ነገር አለ በማለት እንዲያወጡና እንዲያወርዱ አስግድዷቸዋል። በታወቁት የፖለቲካል ኢኮኖሚክስና ዓለም አቀፍ ፖለቲካ ተመራማሪና የሶስተኛው ዓለም ህዝብ ተቆርቋሪ በሆኑት አሜሪካዊው ፕሮፌሰር ጄምስ ፔትራስ እንደዚህ ዐይነቱ አጸያፊ የአፍሪቃ መሪዎች ድርጊት በግብዣ የሚካሄድ(Colonialism by invitaion) የቅኝ ግዛት አድርጉኝ ጥሪ ብለው በትክክል ይጠሩታል። በብዝዎችም ትክክለኛ ትንትና ይህ የአፍሪቃ መሪዎች ድርጊት ግሎባላይዜሽንና እንደዚህ ዐይነቱ መዋዕለ-ነዋይ የሚያመጣውን ህብረተሰብአዊና የአካባቢ ጠንቅ ለመረዳት ካለመቻል በጭፍን የሚካሄድ ድርጊት ነው ብለው ያስቀምጡታል። በትክክልም እንደዚህ ዐይነቱ በቀጥታ ውረሩኝ ማለት ከአፍሪቃ በስተቀር በላቲን አሜሪካ ወይም በአሺያ የሚካሄድ አይደለም። ብዙ የላቲን አሜሪካ አገሮች ከዓለም አቀፍ ኩባንያዎች ቁጥጥር ስር ለመውጣትና ሀብታቸውን ለመቆጣጠር ከፍተኛ ጥረት እያደርጉ ነው። የአፍሪቃ መሪዎች ግን እጅግ በሚያሳፍር መልክ እንደከብት እየተነዱና ህዝቦቻችውንም ወደ ባርነት እየለወጡ በመሄድ ላይ ናቸው።

በ19ኛው ክፍለ-ዘመን ቅኝ ገዢዎች ወደ አፍሪቃ ሲመጡ በመጀመሪያ ደረጃ ይወስዱ የነበረው እርምጃ የየአገሩን ገበሬ ከመሬቱ ማፈናቀል ፣ ውይም ደግሞ ከዚህ በፊት ያርስ የነበረውን ሰብል ትቶ ወደ እናት አገር ወይም ወደ አውሮፓ አገሮች የሚላኩና እዚያው በፋብሪካ የሚፈበረኩ ሰብሎች ላይ ብቻ እንዲሰማራ ነበር። በዚህ ዐይነቱ ወረራ ፣ የማፈናቀልና ገበሬውን በተወሰኑ ሰብሎች ላይ ብቻ እንዲሰማራ ማድረግ ፣ ወደ ቅኝ ግዛትነት በተለወጡበት አገሮች ውስጥ ፣ የስራ ክፍፍል እንዳይዳብር ፣ ለስራ ክፍፍል መበልጸግ የሚያገለግል የንግድ መስክ እንዳይሰፋፋ ፣ ለምርት ማደግና ለንግድ መስፋፋት የሚያገልግል የባንክና የክሬዲት ስይስተም እንዳይቋቋምና እንዳያድግ ፣ ለመጠቀ ባህል የሚሆኑ ከተማዎች ከአማመሩ ህንፃዎች ጋር እንዳይሰሩ ማገድ ነበር። የየአገሩን የመንግስት ማሺኖችና የፖለቲካ ስርዓቱን ለቅኝ ገዢዎቹ እንዲስማማ በማዋቀር ፣ ሰፊው ህዝብ ጭንቀላቱ እንዳይከፈት ፣ የትምህርት መስኩ ቀጭጮ እንዲቀርና ፣ መጠየቅና ማሰብ የሚችሉ ሰዎች ብቅ እንዳይሉ የቅኝ ግዛት አስተዳዳሪዎች ያልተከሉት እንቅፋት ይህ ነው አይባልም። በዚህ መልክ የተዋቀረው ሰርዓት የቅኝ-ግዛቶቹ እንደ ህብረ-ብሄር እንዳይዋቀሩና ህዝቡም አገሩን አገሬ እንዳይል ከፍተኛ መሰናክል አዋቀረውበት ነበር። ይህ ዐይነቱ ስርዓት ስር በመስደዱ በተለይም ኤሊቱ ብሄራዊ ስሜት እንዳይኖረው አድርጓል። ለአህጉሪቱ ኋላ መቅረትም አንደኛውና ዋናው ምክንያት ሊሆን ችሏል።

ዛሬ በ21ኛው ክፍለ-ዘመን ብዙ የአፈሪቃ መሪዎች የቅኝ-ግዛት ጥሎ ከሄደው አስከፊ ሁኔታ ምንም የተማሩ አይመስሉም። ይህች ዓለም የውድድር ዓለም መሆኗን ተገንዝበው በቁጭት በመነሳት ለህዝባችው መልካማ አርአያ በመሆን የስለጣኔውን ፋና ሲያሳዩት አይታይም። በተቃራኒ ግን እኛ መሬታችንን ማልማት አንችልም ፣ ያለንን ጥሬ-ሀብትም በስነ-ስርዓት መጠቀም አንችልም በማለት መሬታችውን ወደ መርዛማናት እንዲለወጡ በማድረግ ላይ ናችው። ዩራኒዩም የሚወጣባቸው አንዳንድ የማዕከለኛው አፍሪቃ አገሮችን እንደ ምሳሌ መውሰድ ይቻላል። አካባቢዎቹ ወደ ፊት ለሰው ልጅም ሆነ ልእንስሳት መኖሪያ የሚሆኑ አይደሉም።

አፍሪቃን እንደገና በመቀራመቱ ሂደት ላይ ፣ ከቻይና ፣ ከህንድና ከአረብ አገሮች ሌላ ብዙ የአሜሪካን ባንኮች ፣ በተለይም ሄጅ ፊንድስ ተብለው የሚጠሩና እንዲሁም ኢንቬስትሜንት ባንኮች ይገኙበታል። ዋናው ዓላማቸውም ጥሬ-ሀብትን በመቆጣጠር የአየር ባየር(Speculation) ንግድ ለማጦፍ ነው። በዚህ መልክ እጥረት ያለ ይመስል ዋጋ እንዲናር

በማድረግ የበለጠ ገንዘብ ለማከማቸት ነው። በዚያው መጠንም የአፍሪቃ ዕድገት ለብዙ መቶ ዐመታት ውድ ኋላ እንዲገፈተር ይገደዳል ማለት ነው። የቻይናና የህንድ ዋና ፈላጎት ከኢኮኖሚ ዕደገታቸው ጋር እጨመረ የህዝባችውን የምግብ ፍላጎት በተከታታይ ማሟላት ነው። ለዚህ ደግሞ ዝም ብሎ የተኛው የአፍሪቃ መሬት አመቺ ነው።

## ተጠቃሚው ማን ነው ?

በብዙ የአፍሪቃ መሪዎቸና የኒዎ-ሊበራል ኢኮኖሚስቶች ዕምነትና የግሎባላይዜሽን ሰባኪዎች ከውጭ የሚመጡ መዋዕለ-ነዋዮች ፣በማንኛውም መልኩ ይሁን የስራ መስክ ይከፍታሉ ፣ በዚያውም በደሞዝተኛው አማካይነት አዲስ ተጠቃሚ ኃይል ይፈጠራል ፤ የተወሰነው ገንዘብም በቁጥባ መልክ ባንክ ሰለሚቀመጥና ይህ ለአዳዲሰ መዋዕለ-ነዋይ በማገልገል አጠቃላይ ኢኮኖሚ ዕድገትን ያመጣል የሚል ነው። ብዙ ጥናቶች(Empirical Studies) እንደሚያረጋግጡት ከሆነ ግን ከፍተኛ ዕውቀትና ቁጥጥር እስከሌለ ድረስ ከውጭ አገር የሚመጡ መዋዕለ-ነዋዮች ለተስተካከለ ኢኮኖሚ ዕድገት አስትውፅኦ ማድረግ እንደማይችሉ ነው። 1ኛ)ሰራተኛው የሚያገኘው ገቢ በጣም ዝቅተኛ ከመሆኑም የተነሳ ሰራተኛው እየገዛ ሊጠቀም የሚችለው ዘመናዊ የኢኮኖሚ ዘርፍ በሚባለው ውስጥ የሚመረተውን ምርት በመግዛት ሳይሆን ኢንፎርማል መስክ በሚባለውና ከእጅ ወደ አፍ ከሚታረሰው መስክ ወደ ገበያ መጥቶ የሚሸጠውን ነው። ሰለሆነም የሰራተኛው ገቢ ወደ ዘመናዊው መስክ የመፍሰስ ዕድል ስለ ማይኖረው ለአጠቃላይ የሀብት ክምችት ሊያገለግል አይችልም።2ኛ) ሰራተኛው የሚያገኘው ገቢ በጣም ዝቅተኛ ከመሆኑ የተነሳ ባንክ ውስጥ ገንዘቡን በቁጠባ መልክ ሊያስቀምጥ አይችልም ፤ ደሞዝም በባንክ አማካይነት ስለማይተላለፍ ባንኮች በቂ ፈሳሽ ገንዘብ ሊያገኙ አይቸሉም። 3ኛ)ወደ አገር ውስጥ የሚገቡት ቴክኖሎጂዎች ያለቁ ስለሆነ በራሳቸው ለቴክኖሎጂ ዕድገት መሰረት ሊሆኑ አይችሉም። ስለሆነም ምርምርና ዕድገት (Research & Development) የሚባሉት ለቴክኖሎጂ መሰረትና ለኢንዱስትሪ ዕድገት እጅግ በጣም አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች አይኖሩም።በዚህ መልክ ደግሞ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሊዳብሩ አይችሉም ማለት ነው። በብዙ ሶስተኛው ዓለም ተብለው በሚጠር አገሮች የምናየው ስርዓትን ይዞ የሚጓዝ ዕድገት ሳይሆን የተዘበራረቀና በቀላሉ ሊቀረፍ የማይችል የማህበራዊና የባህል ቀውስ ነው የሚፈጥረው።

ስለሆነም ይህ ዐይነቱ መዋዕለ-ነዋይ የሚጠቅመው በመንግስት መኪና ላይ የተቆናጠጠውን የገዢ መደብና ጥቂቱን ኢሊት ብቻ ነው። በቀላሉ በጉቦ በመታለል በደንብ ያለተጠና ፈቃድ በመስጠት በአጭር ጊዜ ውስጥ ይደልባል። ይህ ዐይነቱ የህብረተሰብ ክፍል ደግሞ ህብረትስብአዊ ሃላፊነት ስለማይሰማው ራሱን ከተቀረው የህብረተሰብ ክፍል በማራቅ ለህብረተሰብአዊ ውዝግብ ምክንያት ይሆናል። ከዚህ በተረፈ ዋና ተጠቃሚው የወጭ ከበርቴው ነው። 1ኛ)ትርፉን በቀጥታ ወደ ውጭ ያስተላልፋል። 2ኛ)የገቢ ታክስ አይከፍልም ፤ ወይም ደግሞ በቢላንዝ ቴክኒክ በማጭበርበር ከውጭ ወደ ውሰጥ ያስገባውን የምርት መሳሪያዎችና ልዩ ልዩ ለምርት የሚያገለግሉ ነገሮች በውድ ዋጋ እንደገዛ ያስቀምጣል። በዚህ መልክ ወጪው ከፍተኛ እንደሆነና ገቢው ደግሞ ዝቅተኛ እንደሆነ ለማሳመን ይሞክራል። 3ኛ)ጥሬ-ሀብቱ በቀጥታ ወደ ውጭ አገር ስለሚላክ ፣ አገር ውስጥ ተጨማሪ ምርት(Value-added)ሊመረት ስለማይችል እንደሰንሰለት መያያዝ ያለበት ዕድገት አይኖርም ማለት ነው። በአጠቃላይ ሲታይ ፣ ይህ ዐይነቱ መዋዕለ-ነዋይ ለኢንዱስትሪ አገሮች የሀብት ክምቸትና የኢኮኖሚ ዕድገት ነው የሚያገለግለው። በአንፃሩ ግን እንደ ኢትዮጵያ የመሰለች አገር ከብዙ አቀጣጫ ዕደገቷ እንዲዛነፍ ይደረጋል። ቀጭጫ እንድትቀር ትገደዳለች።

ከዚህ ስንነሳ የውጭ አገር ኢንቬስተሮች የሚረባረቡብት የእርሻው መስክ በየትኛውም ዐይነት ይሁን ለኢትዮጵያ ዕድገት የሚያመጣው ጥቅም የለም። የእርሻው መስክ ደግሞ እንደ ህዝብም መመገቢያና ለኢንዱስትሪው መስክ እንደ ጥሬ-ሀብት አቅራቢ ካልታያና እንክብካቢ ካልታደረገለት ፣ የውጭ ከበርቴዎች ተቀጥያ ዘርፍ ነው የሚሆነው ማለት ነው። በተጨማሪም በዚህ መልክ የሚካሄደው ወረራ በየአካባቢዎች ልዩ ልዩ የዕደ-

ጥበብ ስራዎችና ሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች እንዳይቋቋሙ ያግዳል። የባህል ዕድገትም አይኖርም ማለት ነው።

## በአካባቢ ላይ የሚኖረው ተጽዕኖ !

ዛሬ በየአገሩ የሚተከሉት ሰብሎችና አበባዎች የተዳቀሉና የላቦራቶሪ ውጤቶች ናችው። በመጀመሪያ ደረጃ አንድ ወጥ ሆነው(Monoculture) ስለሚተከሉ በአካባቢ ሌላ ሰብል ወይም አትክልት የመዝራት ወይም የመትከል ዕድል አይኖረውም። በሁለተኛ ደረጃ ፣ ማንኛውም የተዳቀለ ሰብል የመሬትን ውስጥ ውሃ የመምጠጥ ኃይሉ ከፍተኛ ነው። በብዙ አገሮች እንደታየው ይህ በራሱ ለድርቀት ምክንያት ይሆናል። ቅጥ ያጣ ዘመናዊ እርሻ የሚካሄድባቸውና በፕላስቲክ ተሸፍነው ሰላጣና ቲማቲም እንዲሁም ሌሎች አትክልቶች የሚተክልባችው እንደስፔይን የመሳሰሉ አገሮች በየዐመቱ በከፍተኛ ድርቅና የውሃ እጥረት ይጠቃሉ። በ70ኛው ክፍለ-ዘመንም ሰሜን አሜሪካ በድርቅ ከመጠቃቷ የተነሳ በአንድ አካባቢ ሰብል እንዳለ ሊወድም ብቅቷል። ስለሆነም እንደገና ለመዝራት ዘር የወሰደችው ክኢትዮጲያ የጂን ባንክ ነው። ሶስትኛ ፣ ይህ ዐይነቱን እርሻ ለማስፋፋት የግዴታ በሰፋት የኬሚካል ማዳበሪያ መጠቀም ያስፈልጋል። ይህ በራሱ አካባቢን መመረዙ ብቻ ሳይሆን ወደ መሬት ውስጥ በመግባት ውሃን ይበክላል። በዚህ መልክ የተመረዘ ወሃ ሲጠጣ ብዙ የጤንነት ቀውሶችን ያስከትላል። በአራተኛ ደረጃ ፣ እንደ ንብ የመሳሰሉትን በመመረዝ ቁጥራችው እንዲቀንስ በማድረግ በማር ምርት የሚተዳደሩ ገበሬዎች እንዲጠቁ ይደረጋሉ። አሁን በጥናት እንደተደረሰበት የንብ ተግባር ማር በመለገስ በቻ የሚወሰን ሳይሆን በጠቅላላው በአንድ አካባቢ ለሚገኙ አፅዋትና ሌሎች አትክልቶች ጠቃሚ ተግባርም እንዳላት ነው።

በተለይም አሁን የተያዘው ፈሊጥ ሽንኮራ አገዳንና  በቆሎ በብዛት መትከል ስለሆነ የግዴታ ጫካ እንዲወድም ይደረጋል። ለአካባቢ ደንታ የሌላችውና ለሰው ጤንነት ምንም ስሜት የማይሰማቸው በጥቂት ገንዘብ እይተታለሉ የሚሰጡት ፈቃድ ከፍተኛ የአካባቢን ቀውስ ማስከተሉ ብቻ ሳይሆን የሰውንም መፈናቀል ያስከትላል። በተጨማሪም እንክብካቤ የሚያስፈልጋቸው የብዙ ዐመታት ዛፎች በመቆረጥ የአካባቢው ውበትም ይጠፋል ማለት ነው። ይህ ብቻ ሳይሆን ፣ ወደፊትም የህብረተሰቡ የምግብ ባህልም ሊበላሽ ይችላል። በተለይም ብዙ ስታርች ያለው በቆሎ በአገራችን ከተስፋፋ ፣ ፕሮቲንና ቢታሚንን ያቀፉ የሰብል ዐይነቶች ቀስ በቀስ እየቀነሱና እየወደሙ ይሄዳሉ ማለት ነው። በደቡብ አፍሪቃ በቅኝ-ግዛት ዘመን በጉልበት በቆሎን ማስፋፋት የተካሄደው ዐይነት ሂደት በአገራችንም በአጭር ጊዜ ውስጥ የማይከሰትበት ምክንያት የለም። ብዙ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት አንድ ወጥ አመጋገብ የማሰብ-ኃይልን እንደሚዘጋ ነው።

ይህ ዐይነቱ አገርን የመቸብቸብ ፖሊሲ የአገዛዙን ግራ መጋባት የሚያሳይ ነው። በተለይም በሚቀጥሉት አምስት ዐመታት ትራንስፎርሜሽን አመጣልሁ እያለ የሚፎክር መንግስት ፣ በዚህ አንድ ወጥ የእርሻ ፖሊሲ እንዴት አድርጎ የተስተካከለ ዕድገት እንደሚያመጣና የህዝባችንን ኑሮ እንደሚለውጥ ነው። ትራንስፎርሜሽን ሲባል ሁለንታዊና ውስጠ-ኃይል ያለው ክንውን ነው። በተጨማሪም የአንድን ህብረተሰብ ፍላጎትና የአካባቢን ሁኔታ የሚያካትትና ተከታታይነት ኖሮት ህብርተሰብአዊ ሚዛን እንዳይናጋ ማድረግ ያለበት ፖሊሲ ነው። የኢህአዴግን የሃያ ዐመቱን የኢኮኖሚ ፖሊሲ ስንመለከት ግን የተምታታበት ብቻ ሳይሆን ሀብትን በስነስርዓት መጠቀም የማያስችልና ፣ የተወሰነውን የህብረተሰብ ክፍል የሚጠቅምና ስግብግብ የሚያደርግ ነው።

## የእርሻ ምኒስተር ተገባርና ኃላፊነት !

በማንኛውም ህብረተሰብ ውስጥ ይሁን አንድ ምኒስተር ኃላፊነቱና ተጠያቂነቱ ለህዝብ ነው። በተሰጠው ኃላፊነት ኃላፊነቱን በመወጣት ለሌሎቸም አርአያ መሆን ያለበት ነው። ከዚህም በላይ ከህዝብ በቀረጥ መልክ በሚሰበሰብ መልክ ደሞዝ ስለሚከፈለው የህዝብ አገልጋይ ነው ማለት ነው። ይህም ማለት ህገ-መንግስቱ ከሚፈቀድለት ውጭና መሃል

ከገባለት ህዝብን በሚገባ ከማገልገል ሌላ ህዝብን የሚጎዳ ነገር ተግባራዊ የማድረግ መብት የለውም።

ይህ በቀጥታ ሲተረጎም የእርሻ ምኒስተሩ ተግባርና ኃላፊነት የህብረተሰቡን የምግብ ፍላጎት በዐይነትም ሆነ በብዛት ማሟላት ነው። ይህም ማለት ህብረተሰቡን ከማንኛውም ጥቃት መከላከል ማለት ነው። የሚዘሩ የሰብል ዐይነቶች አንድ ወጥ እንዳይሆኑ የአካባቢ ሚዛን ተጠብቆ ሰብል እንዲዘራና በወራቱ በስነስርዓት መሰብሰቡን መቆጣጠር አለብት። ይህ ብቻ ሳይሆን ገበሬው ለልፋቱ ተመጣጣኝ ዋጋ ማግኘቱን ማረጋገጥና ፣ በተለይም ከውጭ በሚመጡ ተመሳሳይ የእህል ዐይነቶች የአገር ውስጥ ምርት ዋጋ እንዳይቀነስ ከሚመለከተው ባለስልጣን ጋር እየተመካከረ አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ ዝግጁ መሆን አለብት። ለምሳሌ ጃፓን ገበሬዋን ለመከላከል ስትል ከውጭ የሚመጣ ሩዝ 500% ትቀርጣልች። ከዚህም ባሻገር የምኒስትሩ ተግባር የደን ሀብት እንዲጠበቅ አስፈላጊውን እንክብካቤ መውሰድ ብቻ ሳይሆን ለማገዶና ለቤት ስራም ሆነ ለሳንቃ እንዲሁም ለልዩ ልዩ ስራዎች ሊጠቅሙ የሚችሉ ዛፎች እንዲተከሉ አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ አልበት። ይህንን በሚመለከት ቢያንስ በየሁለት ዐመቱ ስለ አገሪቱ የደን ጤንነት ጉዳይ ተጠንቶ በሪፖርት መልክ እንዲቀርብ ማድረግ አለበት። ይህንን ማድረግ የማይችል ምኒስተር ኃላፊነቱን ሊወጣ የሚችል አይደለም ማለት ነው።

ከዚህ ከላይ ባጭሩም ቢሆን ከተዘረዘረው ሁኔ ስንነሳ የድሮውም ሆነ ያሁኑ ምኒስተር ኃላፊነታችውን ሊወጡ የቻሉ አይደሉም ማለት ነው። ህዝቡንም በስርዓት ለማገልገል የሚችሉ አይድሉም ማለት ነው። በቅርቡ ህንድ ድረስ ሄዶ የተፈራረመው ምኒስተር የኩባንያውን ጥቅምና መብት የሚያስጠብቅ ነው የሚያስመስለው። የኢትዮጵያን ገበሬና የተጠቃሚውን ህዝብ መብትና ጥቅም ለመጠበቅና ለማስጠብቅ የሚችል አይደለም። እንደዚህ ዐይነቱ ምኒስተር ጀርመን ወይም ሌላ የምዕራብ አውሮፓ አገር ቢሆን ኑሮ ከኃላፊነቱ ቶሎ እንዲነሳ ይደረጋል። ችግሩ ግን ዲሞክራሲያዊ ስርዓት በሰፈነበትና የአስተዳዳሪዎች ንቃተ-ህሊና በጎለመሰበት አገዛዝ ስር አይደለም ህዝባችን የሚተዳደረው። ህዝቡ ራሱን ለመከላከል የግዴታ ድርጅቶች ማቋቋም አለበት። ዕውቀት ያላቸው ሰዎች እየገቡ ምክር መስጠት መቻልና እንዴት መብቱን እንደሚያስጠብቅ ማስተማር አለባቸው። በተረፈ ህዝቡ አገር ሲቸበቸብ ዝም ብሎ የማየትና የመቀመጥ መብት የለውም። የኋላ ኋላ የሚጎዳው ተተኪው ትውልድ ነው።

ፈቃዱ በቀለ